የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፹፫
አዲስ አበባ–ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 83
ADDIS ABABA– 18th July, 2003


ማውጫ


የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፱/፲፱፻፺፭ ዓ·ም
የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት
(ማሻሻያ) ደንብ ...................................... ገጽ ፪ሺ፫፻፴፪


CONTENTS


Council of Minister Regulation No.89/2003
The Customs Tariffs council of ministers Amendment Regulation ...................................... Page 2332


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፱/፲፱፻፺፭
## የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በዓለም አቀፍ የተዋሀደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓት ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፹፭ አንቀጽ ፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፹፱/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

ከጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፪/፲፱፻፹፭ (እንደተሻሻለ) ጋር ተያይዞ የሚገኘው የጉምሩክ የዕቃ ቀረጥ ሥርዓትና ተመን ሁለተኛ መደብ እንደሚከተለው ተሻሽሏል ።

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 89/2003
## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO AMEND THE CUSTOMS TARIFFS REGULATIONS

This regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 4 of the International Convention on the Harmonized Commodity Description and coding system Ratification Proclamation No. 67/1993.

1. *Short Title*

   This Regulation may be cited as the "Customs Tariffs Council of Ministers (Amendment) Regulation No.89 2003"

2. *Amendment*

   The Second Schedule of the Customs Tariffs Classification System of goods and Rates attached to the Customs Tariffs Council of Ministers Regulation No. 122/1993 (as amended) is hereby further amended as follows:

፩· <u>አንቀጽ ለ(፬)ሀ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ለ(፬)ሀ ተተክቷል።</u>

"፬· የኢትዮጵያ መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ የዕርዳታ ድርጅቶች ስለሚያስመጧቸው ዕቃዎች

(ሀ) የኢትዮጵያ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ የዕርዳታ ድርጅቶች የሚያስመጧቸውን የልማት መሣሪያዎችና ዕቃዎች የገቢዎች ሚኒስቴር ፤ አግባብ ካለው የፌዴራል መሥሪያ ቤት ወይም የክልል መስተዳድር ቢሮ በሚቀርብለት የፕሮጀክት የስምምነት ሠነዶች መሠረት ቋሚ የልማት መሣሪያዎችና ዕቃዎች መሆናቸውን አረጋግጦ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ይፈቅዳል።"

፪· ንዑስ አንቀጽ ፲ ተሠርዞ በሚከተለው ንዑስ አንቀጽ ፲ ተተክቷል ።

"፲· <u>ሥልጣን</u>

(ሀ) የገቢዎች ሚኒስቴር በዚህ ደንብ መሠረት የኢትዮጵያ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ የዕርዳታ ድርጅቶች የሚያስመጧቸው የልማት መሣሪያዎችና ዕቃዎች ከፕሮጀክቶቹ ጋር የሚዛመዱ መሆናቸውን ፕሮጀክቱ የሚመለከታቸው የፌዴራል መሥሪያ ቤቶችና የክልል መስተዳድር ቢሮዎች የሚያቀርቡለትን ሠነድ መርምሮ በማረጋገጥ ፤ የቀረጥ ነፃ መብቱን አፈጻጸም የማመቻቸት ኃላፊነት ተሰጥቶታል።"

<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከ ነሐሴ ፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም·

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

1. Article B(4) a is hereby deleted and replaced by the following new Article B(4)a.

"4. Goods Imported by Agencies of the Ethiopian Government and Non-Governmental Aid Organizations.

(a) Ministry of Revenues shall permit duty free entrance of Capital Goods and machineries imported by Ethiopian government agencies and non-governmental agencies after ascertaining that they are fixed capital goods and machineries, based on the project and contract documents submitted to it by the appropriate federal agency or regional government bureau."

2. Sub-Article 10 is hereby deleted and replaced by the following new Sub-Article 10.

"10. Responsibility

(a) The Ministry of Revenues is hereby entrusted with the responsibility to facilitate the implementation of the duty-free privilege granted hereunder by way of ascertaining, after examination of documents sumitted to it by federal agencies and regional government bureau concerned with the project, that capital goods imported by agencies of the Ethiopian Government and non-governmental aid organizations are related with the given project as required under this Regulation."

3. *Effective Date*

This Regulation shall enter into force as of the 12th day of August 2003.

Done at Addis Ababa, this 18th day of July, 2003.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE